# የቀይ መብራት ፖለቲካ፣ የሽንፈት ወልፍና የመፈንገል ልክፍት

ከ ሀማ ቱማ

በሆነው የሂደት ምስጢር ዓለም ከነግሳንግሱ አለሁ ብሎ ሲገኝ ጀምሮ እውን የሆኑ ክስተቶች ዛሬም ህይወት ያልነውን ኑሮ ማጀባቸው አልቀረም:: ሐጢያትና ገበና፣ ውርደትና ሰለባነት:: የሐጢያቱ ተጠያቂ ማን ይሆን ማን ገና አከራካሪ ቢሆንም ግማሹ ሔዋንን ቀሪው ደግሞ ቋንቋ አልባ እባቡን እየረገሙ መቀጠላቸው የሚታወቅ ነው:: ወደ ዘመኑ ፖለቲካ ስንመጣ ደግሞ ድል አድራጊው የህቅ ባለቤት እየሆንና ተሸናፊው ነጋ ጠባ እየተወገዘ ወይም በጥፋተኛነት--የወደቀ ዛፍ ምሳር ይበዛበታል ነውና-- መከሰሱ ወይም መወንጀሉ  የተለመደ ነው:: በሀገራችን ፖለቲካ ደግሞ ባለሥልጣኖቹ የብዕር ኩሊዎች ወይም ቅጥረኞችን በማሰለፍ ታሪክ ሰሪዎችንና ጀግኖችን እያንኳሰሱ ሲከትቡ ቆይተዋል:: ከኔ ሌላ የማን ስም ተደንቆ ባዩ አፄ ለምሳሌ በቢትወደድ መኮንን አማካኝነት አፄ ቴዎድሮስን በአውሬነት መድበው አፅፈዋል:: የልጅ ኢያሱም ታሪክ እንዲሁ በሀቀኛ መልኩ ብዙውን ጊዜ አልቀረበም:: ወዘተ ወዘተ

ይህን መንደርድሪያ ካደረግኩ በኋላ ወደ ዋና ነጥቦች ስመለስ ፖለቲካ በደፈናው የእውር አጥር ሆኖ ሲዘበራረቅ ማየቱ የግድ አለመሆኑን መረዳት እንችላለን:: ቀይ መብራት በወዲህ ቁም አትንቀሳቀስ ሲሆን በሌላ መልኩ ደግሞ ማንም ሊገባበት የሚችልበትን የዝሙት፣ የመሸታና የዳንስ--የዳንኪራ ቤትን የሚያመለክት ነው:: ሁሉም የሚገባበት፣ ሁሉንም የሚቀበልና የሚያስተናገድ ቤት:: ፖለቲካን በዚህ መልኩ የሚወስዱት በርከት ሲሉ የፖለቲካው መስክ የሁሉም መንቦጫረቂያ ይሆንና ምስቅልቅሉ ውዥንብርን አንግሶ ለሕዝብ ጠላት አመቺ ሁኔታ ይፈጠራል :: አላፊ አግዳሚውን፣ ሆድ አምላኩና ቅዕል ፈታዩን፣ ጡረታ ወጪውንና ጨቅላውን፣ ንዋይ አሳዳጁንና ተክለ ሰብ አፍቃሪውን፡ ያልበሰለውንና እንክርዳዱን፣ ጥራዝ ነጠቁንና ፈረንጅ አምላኩን፣ ጥይት ሲጮህ በርጋጊውንና አስመሳይ ተጋዳዩን በአጭሩ ሁሉንም ተቀብሎ ዕልልታ የሚያቀልጠው ፖለቲካ ለሀገርም ለሕዝብም የሚበጅ አይሆንም:: ዛሬ ከትላንቱ መማር አቅቶን ሰላም እንዴት አደራችሁ ያለን ተጓዥ ሁሉ መሪያችን ብለን ተቀብለን የምናጨበጭብ ከሆነ ከጉድ ያውጣን:: ትላንት ወዲያ መጥምቁ ዮሐንስ ነኝ ያለንና ትላንት ሀሳዊ መሲህ መሆኑን ቁልጭ አድርጎ በተግባር ያሳየንን ዛሬ ሐዋርያና የስርየታችን ቁልፍ አድርገን ከወሰድን ጥፋተኛው እኛው ነን::

ታዋቂ የፖለቲካ መሪ በአንድ  ወቅት ሰው ይቀየራል ያሉት በተወሰነ ደረጃ ሀቅነት ቢኖረውም፣ በተስፋ ለለውጥና ለመሻሻል መጣር ቢገባንም ብዙ ሰዎች ያደቆናቸው ሰይጣን በክፋቱ ጎዳና እያቀሰሳቸው ሲሄድ መታዘቡ ግድ ሆኖብናል:: ትላንት ወንዝ በሌለበት ድልድይ ሊሰሩ ቃል ገብተው የዋሹት ዛሬ  ጎርፉ ሲመጣ መጠሊያ ሊሰጡን መጠበቅ የለብንም:: ትላንት የላባችንን

ፍሬ ገንዘብ ወስዶ ያባከነው ዛሬ አዋጡ ሲል ገንዘቡን ለቁም ነገር አውላላሁ ሲል ማመን የጠያቂ ውን ብልጠት ሳይሆን የሰጪውን ጅልነት አመላካች ነው፡፡ መጠጥና ሴላም ሊሸጡ የተነሱት ሁሉ ንም ና ብለው በሞቀ መንገድ ቢያስተናግዱ ምክንያታቸውና ግባቸው ግልፅ ነው፡፡ በፖለቲካው መስክ ግን አላፊ አግዳሚውን፤ የፖለቲካ ደላላውን ሁሉ ማስተናገድና መሪ ብሎ ማቀፉና መከተ ሉ ውድቀትን አሊያም የከረረ ብስጭትን ማስከተሉ የማይቀር ነው፡፡ በፖለቲካ ቀይ መብራት ለሁሉም መስተንግዶ ሳይሆን ቆም በል፤ እስቲ ቆም እንበል የሚል መሆን አለበት፡፡ ቆም ብሎ ያለፈውን ተመክሮ መገምገም ያስፈልጋል፤ ቆም ብሎ ምርቱን ከግርዱ መለየት ያስፈልጋል፡፡ ምንኛ ቅዕሎች ቢደረድርና ጃሎ ቢል የማጀት አውደልዳይ ወይም የፍርሀት ምሳሌ ጀግና መሪ ና አዋጊ ሊሆን አይችልም፡፡ በጥባጭነት በደሙ የሚንሸራሸርበት የሚመስለውም ረጋ ብሎ አሰባ ሳቢ ሊሆን መጠበቅ የለበትም፡፡ ከሰው ደግሞ ከአቅሙና ከጠባዩ በላይና ባሻገር ሲጠበቅ የተወጠ ረው ይበጠሳል፡፡ ይህን ሁሉ በረጅም የትግል ተመክሮ ሕዝባችን ያየውና የታዘበው ነው፡፡ ልኩንና አቅሙን፤ ጠባዩንና ችሎታውን መትሮ በዚያው መልክና ልክ መያዝ እንጂ በወር እስር ግለሰቡን ማንዴላ ማለቱ፤ ተክለሰብ ማጠንጠኑና ለሆዱ ያደረውን ለሀገር ሟች ብሎ መውሰዱ ሆነ ለረሽ/ ገንጥል ጥይት የሚበረግገውን--ልጥ አይቶ የሚዘለውን-- የድብልቅልቅ ጦርነት ጀግና መሪ-- ኮማንደር አድርጎ መውሰዱ መጨረሻው አያምርም፡፡ በፖለቲካ ቀይ መብራት መድረኩን በአልባ ሌና አፍቅሮ ንዋይ ባጠቃቸው ወይም ዝናን ፈላጊዎችና ሙቱልን ባዮች የሚሞላ የዳንኪራ ቤት ሊያደርግ መፈቀድ የለበትም፡፡ የቀይ መብራት የመሸታ ቤት ፖለቲካ ሀገርን ይጎዳል፡፡ የፖለቲካ አመንዝራነት ደግሞ ከዘመኑ በሽታ በከፋ ሀገርና ሕዝብን የሚያጠፋ ነው፡፡

ወያኔ በመጪው ግንቦት ምርጫ ብሎ ሊያካሂድ በተነሳው ቧልት አይሉት ተዝካር ገብቶ ከመገኘ ት በፊት ቆም ብሎ በጥሞና የ 1997ቱን ምርጫ ሂደትና ውጤት፤ የተገኘውንም ተመክሮ መገም ገም አስፈላጊ ነው፡፡ ሊታገል ለተነሳ ኃይል ቅርሱን መመርመር ትጥቁን ማዳበርና ራሱን ማጠናከ ር ነው፡፡ ቢያንስ ያለፈውን ስህተት አይደግምም፤ ባለፈው ለውድቀት የዳረጉትንም አሰራሮችና መሪ ነን ባዮችንም ዳግም በሥራ አያውልም፡፡ ከሰው ስህተት ከብረት ዝገት ባይጠፋም ጠመንጃ ተፈታቶ ሁሌም በጊዜ ከተወለወለ ዝገት አያጠቃውም፡፡ ድርጅትም ትግልም ራሱን ከገመገመ ከፖለቲካዊ ዝገት ራሱን ይከላከላል፡፡ ዛሬ አንዳንዶች የነገሮችን ውል ስተው ችግሩ ከዓመታት ቆጠራ ጋር የተያያዘ አስመስለው ለማቅረብ ቃላት ይደረድራሉ፡፡ በቆራጥነትና በጀግንነትና ለዚህ ም መሠረት ለሆነው ንቃት ዓይነታ ምሳሌ የነበሩት ደጃዝማች ታከለ ወልደ ሐዋርያት ወጣት አልነበሩም--ልባቸው ግን ሙሉና የወጣት ነበር--ባለወኔ፡፡ በወጣትነቱ ሀሞቱ የፈሰሰ ካልን ዘንዳ ደግሞ መለስ ዜናዊም ምሳሌ ነው፡፡ የሰው ብልህነት ከዕድሜው ጋር ሳይሆን የተያያዘው ከጭንቅ ላቱ፤ ከአስተሳሰቡ፤ ከአስተዳደጉ ነው፡፡ የዕድሜ ፀጋነትም ከዓመት ቆጠራ ጋር ሳይሆን ከተመክሮ ና አቅዋም ጋር የተቆራኘ ነው፡፡ ጭንቅላት ስንልም የማሰብ ችሎታን እንጂ የተምሯል ታርጋን አለመሆኑም ግልፅ ነው፡፡ ችግሩ ፖለቲካው ዝገትና ዝቅጠት ከሚባለው መንደር መፈለግ ያለበት ነው ማለት ነው ፡፡ ተደጋግሞ እንደተባለው ጠላትህን ካወቅከው ታሸንፈዋለህ --በበለጠ ግን ራስ ህን ካወቅክ አይበገሬ ትሆናለህ፡፡ ቆም ብሎ--ቀይ መብራትን በዚህ መልኩ አብርቶ--ያለፈውና

ያለውን ሁኔታ መመርመር ተገቢና አስፈላጊ ነው፡፡ ይህ ከተደረገ ነጋ ጠባ የወያኔ ተንኮል ሰለባ መሆን ይቀራል፡፡ ይህ ከተደረገ ሀቀኛ ታጋዩንና ፀረ ወያኔውን ከአስመሳዩና በሰሞኑ አነጋገር ከኮሾው ተቃዋሚ መለየት ማበራየት ይቻላል፡፡ የሕዝብ ጎራም ይፀዳል፡፡ የፀዳ ጎራም የተጠናከረ ይሆንና ለፀረ ወያኔው ትግል ልንመካበት እንችላላን ማለት ነው፡፡

የሚታገል ድርጅት ሆነ ሕዝብ የሽንፈት ወልፍ ሊኖረው አይችልም፤አይገባምም፡፡ ወልፍ የያዘው ይመስል ግን ለሽንፈት የዳረጉንን አቋሞችና ውሳኔዎቸ ወይም ልምዶች መደጋገሙ ቢያስጠይቅ ሲያንስ ነው፡፡ ብዙ ጊዜ የተሞከሩ የህብረት ግንባር ምስረታ ሂደቶች ስህተቶችን ሲደጋግሙና በዚህም የተነሳ ሲዳከሙ አይተናል፡፡ ትግልን ሊመሩ ቀርቶ ለመመራትም ችሎታ ውና ብቃቱ የሚያንሳቸው የመድረክ ፋኖዎች ሆነው ትግሉ ሲጠጥር ግን ሕዝብን አሳልፈው ሲሰጡ በተደጋጋሚ  ምሩን እያልናቸውና ስህተት እየፈፀምን ተጎድተናል፡፡ ትላንት ጦርነትን የሰሩብንን ዛሬ ጦርነትን ሊሰሩልን በየዋህነት እንጠብቃለን፡፡የአባትን ገዳይ አባዬ ማለት ዓይነት፡፡ ባዕዳን የእኛ ሕዝብ ጉዳይና ሰቆቃ ጉዳያቸው አለመሆኑን እያወቅን፤ በቁሰላችን ላይ ጨው መነስ ነሱ ደስታቸው መሆኑ እየተነገረን፤ከሙሶሊኒ ወረራ ጊዜ ጀምሮ እንኳን ደግመን ደጋግመን ያወቅ ነው ሆኖ በ1997ም ሆነ ዛሬ በ 2002 ዓ.ም. ይህንኑ ስህተት በመድገም ከባዕዳን ስርየትና ነፃነት ይመጣል ብለን ስንጠብቅ እንታያለን፡፡ ዛሬ ጉድ አደረጉን ብለን የምናዝንባቸው ሀገሮችም ሆኑ ግለሰቦች ትላንት ወይ ከጠዋቱ ከእኛ ጋር አለመሆናቸውን፤ ለእኛ አለመቆማቸውን አሳይተውን ነበር፡፡ በእጅ ያልገባ ዱላ እባብ አይገድልም የተባለውን መረዳት ሲገባን ላም አለኝ በሰማይን ማንጎራጎሩን ከመረጥን ለሚደርሰው ጉዳት ያው ተጠያቂ ራሳችን መሆናችን አይቀርም፡፡ ሰባቱ ስትወድቅ ስምንቱ ተነሳ ተባለ እንጂ ሰባቱ ስትሳሳት ስምንተኛም ጨምር አልተባለም ነበር፡፡ ታዲያሳ ምን ነካን? እውን የመሸነፍ ወልፍ ይዞናል? ስቃይና መከራን ለምደናል? ጫንቃችን ለጭቆና ተመቻችቷል፤ደልቧል?

የወያኔ አገዛዝ በሕዝብ ላይ የመጣ መቅሰፍት መሆኑን ዛሬ አሌ የሚል ካለ  ከህቅም ከኢትዮጵያ ም የተጣላ ነው መባል አለበት፡፡ በደም ግብር ታፍሮና ተከብሮ የቆየውን መሬት፤ኢሕአፓም ራሱ ከሱዳን ጋር የተጋጨበትን የቋራ መሬት ወያኔ ለሱዳን አሳልፎ ሰጥቷል፡፡ የክህደት ክህደት፡፡ተጨማሪ ግዛት እስከ ጋምቤላ ድረስም አሳልፎ ለመስጠት ተዘጋጅቷል፡፡ ወያኔ ቀደም ሲልም የጎንደርና ወሎን መሬት በጉልበቱ ወደ ትግራይ አስገብቶ በማካለል ዛሬ ሁመራን ወዘተን " መሬቴ የግሌ የትግራይ" ብሎ ይበዘብዛል፡፡ ሀገር መሸጡን በመቀጠልም ለአረቡ ለቻይናው ለህንዱ ብዙ መቶ ሺ ሄክታር መሬትን አሳልፎ ሰጥቶ ሰዎቹ የሚያመርቱትን ወደ ሀገራቸው እንዲያጓጉዙ ፈቅዶላቸዋል፡፡ ዘረኞቹ የመሬት ተከናታሪዎች ደግሞ መብት አልባውን ሠራተኛ እስከ መደብደብ ድረስ መብት በወያኔ ተሰጥቷቸዋል፡፡ ግብፅ ሳትቀር የዚሁ የለም መሬት ተቀራማች ሆናለች፡፡ ይህ ውርደትና ቅሌት ሲፈፀም ሕዝብ በዝምታ ካየ ወያኔ ቡችላ ቢጮህ አንበሳ ዞር አይልም በሚል ዕብሪት በህገ ወጥና ፀረ ኢትዮጵያ ድርጊቱ ይቀጥላል እንጂ አያቆም ም፡፡ ተመሳሳይ የመሬት ልገሳና ዝርፊያ በማዳጋስካር ተሞክሮ በሕዝብ ተቃውሞ የተነሳ ተሰርዟ

ል። በሌሎች ሀገሮች የኑሮ ውድነትን በመቃወም ሰልፍ ያካሄዱና ተቃውሞ ያሰሙ ሕዝቦች ዋጋ ን አስቀንሰዋል። የኢራን ሕዝብ የተጭበረበረ ምርጫን በመቃወም ደሙን ካፈሰሰ በኋላ በቃኝ ተሸነፍኩ ሳይል በቆራጥ መሪዎቹ አማካኝነት ዛሬም መሰዋዕትነትን እየከፈለ ትግሉን ቀጥሏል። ያዝ ለቀቅ ሳይሆን ጨበጥ ጠበቅ የሆነ ትግልን ውጤታማነት ደግሞ በእኛም ተመክሮ ያየነው ነው። ሁናቴው ሲጠጥር አውጪኝ እግሬ የማይሉ መሪዎችም ያስፈልጋሉ። መሠረታዊው ነጥብ ናትምህርት በተለይ የራስን ሀገር በራስ ማስከበርን ይመለከታል። አረመኔው ቡድን ከጊዜ ወደ ጊዜ ግፍን በግፍ ላይ እየከመረ በሀገርና በሕዝብ ላይ ሲቀልድ --በሽክም የሚሄድ የከተማውን ርቀት አያውቀውም ነውና--፤ በዚሁም ሲቀጥል፤ በሙስና ሲጨማለቅ፤ መረን ሲያጣ፤ ይሉኝታን ሲያደርግ ባዳ በዝምታ ማየቱ ተፈለገ አልተፈለገ በወዶ ገባ ባርነት ሊወሰድ መቻሉንም መቀበል የግድ ይሆናል። ሀገርን ለማስከበር፤ መብትን ለማስከበር ሕዝብ መነሳት መታገልና ለአረመኔወም አገዛዝ ሆነ ለደጋፊዎቹ ባዕዳን አይበገሬነቱን ማሳየት አለበት። ባለቤቱ ያቀለለውን አሞሌ እንዲ ሉ የተከበረች ሀገር ዛሬ የሱዳን ሳይቀር መጫወቻ ስትሆንና ተጨማሪ ቅሌትና ውርደት በወያኔ አጋፋሪነት ሲውጠነጠን መቸስ ማል ጎደኒ -ምን ማረግ ይቻላል-- ብሎ በከንፈር መጠጣ ለመቀበል ጎንበስ ማለቱ ከሰፈነ ወዮላት ለኢትዮጵያ ማለት አለብን። በአጭሩ የሽንፈት ወልፍ አልያዘንም ካልን ለድል መታገል፤ ለመብትና ለሀገር መዋደቅ አለብን ማለት ነው። ይህ ትግልም ብዙ መሰዋዕትነትን ሊጠይቅ ይችላል፤ ጊዜም ሊፈጅ ይችላል፤ ግን መደረግ-- መጀመር መጠናከ ር ያለበት ትግል ነውና ልጆቻችን ውርደትን ከመውረስ ይድናሉ። ድል የለመድን ሕዝብ መሆና ችንንም ዳግም በዓለም ደረጃ እናስመሰክራለን።

ይህ ሳይሆን ቀርቶ ውሀ ውስጥ ከኖርክ ከአዞ መላመዱ አይከፋም በሚል ፈሊጥ፤ የአባትህ ቤት ሲዘረፍ አብረህ ዝረፍ በሚል ብልጣ ብልጥነት፤ ከመሞት መበርከት የሚል አጓጉል የባርነትን አቀንቃኝ ምሳሌ በመደጋገም፤ አቅምን አውቆ መኖር ጥሩ ነው የሚለውን የባረቀ ዘፋኝ ስንኝ በማጀብ ለጠላት መጎንበስና ሀገር ስትጮህ ጆሮን መዝጋት ይከተላል። ተቃዋሚው የለም ተፎካካሪ ነህ በሉኝ ሲል፤ጠላት ማለት እርም ነው ብሎ ሲምል ሲገዝት፤ የሚታገሉትን ሲያብጠለ ጥል፤ገዢዎቹን ሲመስል ማለትም የእኔ ብጤውን ወይም ሰፊውን ሕዝብ ሳይሆን የሕዝብን ጠላት ቀርቦ ሲታይ፤ የሀገር መከራ ቀላል አይሆንም። ሕዝብ ሀገሩንም ራሱንም ማመስከበር የሚችለው በአመፅ እንጂ እጅን በመስጠት አይደለም። የሞቃዲሾ ሕዝብ በአንዲት ሌሊት ከሺ በላይ ህይወት ቢገብርም ወደ 18 አሜሪካኖችን ገድሎ የተወሰኑትን ሬሳ አሸዋ ለአሸዋ ሲጎትት በወራሪ ዎቹ ላይ የበላይነትን ተቀዳጅቷል። አወቅን የሚሉ አንዳንዶች ዛሬ የትጥቅ ትግል ዘመኑ አልፏ ል ብለው የሚታየውን ሀቅ አናይ ቢሉም ዳርፉር ሱዳን አልን ዩጋንዳ፤ ፊሊፒንስ አልን ኮሎምቢ ያ፤ ሶማሊያ ተባለ የመን፤አፍጋኒስታን ኢራቅ ወዘተ የትጥቅ ትግል--ዓይነቱ ቢለያይም--ተፋፍ ሞ ይገኛል። ለነገ ዛሬ ይዘጋጃሉ ተብሏልና የዛሬውን ሁኔታ ስንመረምር ነገ የአመፅና የብረት ትግ ል መስፋፋት--በአፍሪቃ ቀንድና በዓለምም ደረጃ-- አይቀሬ መሆኑን እንገነዘባለን። የነገ ባለቤቶ ች የመፈንገል ልክፍት ያጠቃቸው ሳይሆኑ የአመፅ እሳት በደማቸው የሚሮጠው ብቻ ናቸው። ሕዝብን በነቂስ ፈንግሎ በባርነት ሊገዛ የተነሳው ዘረኛው ወያኔ የኢትዮጵያ ሕዝብ የመፈንገል

ልክፍት እንደማያጠቃው ሊረዳ የሚችለው በሚገባው ቋንቋ ትምህርቱን ሲጋት ነው፡፡ በሰፌው ስናየው ደግሞ ሕዝብ የመጣበትን መቀበል፣ በዝምታ መገዛት፣ ለባርነት መዳረግ፣ ለሚጎረብጠው መመቸትና ታዛዥ መሆን የለበትም፡፡ መሪህ ነኝ ላለ ሁሉ ማጨብጨብ፣ አንቱታውን ዳሽንን ማሳከልና ዴሞክራሲን ማፈን፣ ግለሰብን ማሳበጥና ራስን ፍፁም ተገዢ ማድረግ ድርጅቶቹንም ትግልንም ሲጎዳ ደጋገመን አይተናል፡፡ ለግለሰቦች ያውም በትግል ገና ላልተፈተኑ ፍፁም እምነትን በመስጠት ከበሬታን ሳይሆን ተገዢነትን ማንፀባረቅ ውጤቱ አሉታዊ ነው፡፡ ዕድላችን ሆኖ ባለፉት ረጀም ዓመታት በላያችን የተሰየሙብን አምባገነኖች የፍርሀት ቋቶችና ነፍሰ ገዳዮች ሆነው ታይተዋል፡፡ ክቡር ሊቀመንበር ቢባሉም ቢወደሱም በዙፋን ላይ የወጡ ቁንጮችና መዥገሮች እንጂ ክቡር ሰዎች ሆነው አልተገኙም፡፡ በሌላ ሁኔታም ገና ከወዲሁ ለጣዖትነት የታጩትም ቢሆኑ ገና በሚገባ መሬት ሰማዩ ሳይጫጫስ ሽብረክ ብለው ከትግል ከመከራ ይሻላል በርጩማ ብለው መገኘታቸውን ታዝበናል፡፡ ለዚህም ነው የመፈንገል ልክፍት ሲያልፍም አይነካን ብለን ክብራችንና ሰብዕናችንን ጠብቀን ለሀገርና ለሕዝብ ወሳኝ ትግላችንን መቀጠል ያለብን፡፡